# በእነ ኢንጂነር ኃይሉ የክስ ፋይል ችሎቱ ትናንት የ5 ሰዎችን ምስክርነት አደመጠ

- ተከሳሾቹ እየተከራከሩና መስቀለኛ ጥያቄም እያቀረቡ ነው

ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል ለመገርሰስ ሞክራችኋል በሚል ተጠርጥረው የፌዴራል ዐቃቤ ህግ ክስ በመሰረተባቸው በእነ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የክስ መዝገብ ትናንት ጠዋት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሁለተኛ ወንጀል ችሎት የምስክሮች ቃል አዳመጠ።

ችሎቱ እንደተሰየመ ዐቃቤ ህግ የተከሳሾቹን ጥፋተኝነት ያስረዱልኛል ያላቸውን ሰባት ምስክሮች በዕለቱ ማቅረቡን ገልጿል። ችሎቱም ዐቃቤ ህግ ምስክሮችን አስር አስር እያደረገ እንዲያቀርብ ታዞ እንደነበር በማስታወስ በዕለቱ ለምን ሰባት ምስክሮችን ብቻ እንዳቀረበ ጠይቋል። ዐቃቤ ህግ በበኩሉ ከችሎቱ ለቀረበለት ጥያቄ በዕለቱ ያቀረባቸው ሰባት ምስክሮች በአንድ ዓይነት ጭብጥ ላይ ምስክርነታቸውን የሚሰጡ በመሆናቸውና በሌላ ጭብጥ ላይ የሚመሰክሩትን በዚህ ላይ ደርቦ ማቅረቡ የማስረጃውን ጭብጥ የተቆራረጠ ስለሚያደርገው ነው ብሏል። ሆኖም ግን ችሎቱ ይህ ምክንያት መቅረብ የሚገባው ከተከላሾች እንጂ ከዐቃቤ ህግ ባለመሆኑ ከሚቀጥለው ጊዜ ጀምሮ ምስክሮችን አስር አስር እያደረገ እንዲያቀርብ ለዐቃቤ ህግ ትዕዛዝ ሰጥቷል።

ከዚህ ትዕዛዝ በኋላ በዕለቱ የቀረቡት ሰባቱ ምስክሮች ቀርበው ቃለ መሀላ የፈጸሙ ሲሆን ምስክሮቹ በችሎቱ ደንብና ስነ-ስርዓት መሰረት እርስ በራሳቸው እንዳይገናኙ ተደርጎ በተራ በተራ በመግባት የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል።

በዚህም መሰረት አንደኛው ምስክር ሰሜን ሸዋ ውስጥ የመ.ኢ.አ.ድ አባልና አደራጅ እንደነበሩ ገልፀው፣ ቅንጅት ውስጥ ሰላማዊ የሆነና ሰላማዊ ያልሆነ የአደረጃጀት ስልት እንደነበር አስረድተዋል። ምስክሩ በማያያዝም «በሰላማዊ መንገድ አደራጅ ነህ» የሚል ወረቀት እነ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ፈርመው እንደሰጧቸውና ሰላማዊ ያልሆነ አደራጅ ተብለው ደግሞ በ1996 ዓ.ም ማሙሸት ከተባለው ተከሳሽ ጋር ተዋውቀው ስራ

መጀመራቸውን ገልፀዋል። በዚህም መሰረት ምስክሩ ስራቸው ፖሊስ ስለነበረ በተከሳሹ በማሙሸት በኩል ሽፍቶችንና የቀድሞ መንግስት ወታደሮችን እንዲያደራጁ መመሪያ ተሰጥቷቸው በዚህም መመሪያ መሰረት ከሽፍቶችና በቀድሞ መንግስት ወታደርና ኮማንዶ ከነበሩት ውስጥ 13 ሰዎችን ማደራጀታቸውን፣ እነዚህ የተደራጁት ሰዎችም የራሳቸው መሳሪያ እንደነበራቸው ለችሎቱ ገልፀዋል። አያይዘውም የመደራጀታቸው ዋና ዓላማ «ኢህአዴግ ምርጫውን እንደማያሸንፍና በመሸነፍም ትግራይን እንደሚያስገነጥል ቢያሸንፍ እንኳ ሰላም ስለማይሰጠን በአጠቃላይም ከስልጣን መወገድ ስላለበት ነው» ተብሎ ከአቶ ማሙሸት እንደተነገራቸውና እሳቸውም ይህንን ላደራጇቸው ታጣቂዎች ማስተላለፋቸውን በሰጡት የምስክርነት ቃል አብራርተዋል።

ምስክሩ፣ የተደራጁት ታጣቂዎች ዋነኛ ተግባርም የኢህአዴግ ባለስልጣናትን መግደል፣ በዚያ መስመር የሚሄዱ ተሸከርካሪዎችንና መሰረተ ልማቶችን ማውደም እንደነበር ተናግረዋል።

ጥር/97 ላይ ከሰሜን ሸዋ ተጠርተው አዲስ አበባ ሁለት ጊዜ መምጣታቸውንና በዚህም ጊዜ አባይነህ ብርሃኑ፣ ሻለቃ ጌታቸው መንግስቴና አቶ ማሙሸት የተባሉትን ተከሳሾች ማግኘታቸውንና ስለተሰጣቸው የማደራጀት ስራ ሪፖርት ተጠይቀው ያቀረቡ ሲሆን እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሦስቱ ተከሳሾችም ሪፖርቱን ካዳመጡ በኋላ የማደራጀት ስራቸውን የበለጠ አጠናክረው መቀጠል እንደሚኖርባቸው በተጨማሪም መሀላቸው ውስጥ ኢህአዴግ እንዳይገባ ጥንቃቄ መውሰድና ተግባራቸው በከፍተኛ ምስጢር ሊያከናውኑ እንደሚገባ ተጨማሪ መመሪያ እንደሰጧቸው ምስክሩ አስረድተዋል። ሚያዝያ/97 ላይ ለሁለተኛ ጊዜ አዲስ አበባ ተጠርተው በመጡበት ወቅት «ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ወደ መንዝ ለቅስቀሳ ሊሄዱ ፈልገው አጥተውሃልና አሁን አግኛቸው» ተብለው በእነ አባይነህ በኩል ከኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ጋር እንደተገናኙ ገልፀው ኢንጂነር ኃይሉም «እኛ እንድታደራጅ የፈለግነው በሰላማዊ መልኩ አይደለም። በሰላማዊ መንገድ ለማደራጀት በቂ ካድሬዎች አሉን። አንተን የምንፈልግህ በያዝከው መልኩ

እንድትቀጥል ነው። እነ አባይነህ በሚሰጡህ መመሪያ መሰረት እንድትፈጽም» ብለው ተጨማሪ መመሪያ እንደሰጧቸው ምስክሩ ለፍርድ ቤቱ አስረድተዋል።

አንደኛው የዐቃቤ ህግ ምስክር ይህን ካስረዱ በኋላ ዐቃቤ ህግ «ለዚህ የማደራጀት ስራ የተደረገልዎት ድጋፍ ምንድነው?» የሚል ዋና ጥያቄ አቅርቦላቸዋል። ምስክሩም «ለኔና ለሽፍቶቹ የተለየ ነገር ባይደረግልንም በተጠቀሰው ተግባር ላይ ተሰማርቼ ስራ ላይ በምሆንበት ጊዜ የውሎ አበል ተብሎ በቀን 75 ብር ይከፈለኝ ነበር» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

ከዚህ በማስከተል ማሙሸት አማረ የተባለው ተከሳሽ ለእኚሁ ለዐቃቤ ህግ ምስክር ፖሊስ ሆነህ እንዴት የፖለቲካ ድርጅት አባል ልትሆን ቻልክ?» የሚል መስቀለኛ ጥያቄ አቅርቧል። ምስክሩ ለዚህ የተከሳሽ መስቀለኛ ጥያቄ በሰጡት ምላሽ በ1993 ዓ.ም የመ.ኢ.አ.ድ አባል ሆኛለሁ። ፖሊስ ሆነህ እንዴት የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ገባህ? የሚለውን ጥያቄ ግን ጠያቂዬ አቶ ማሙሸት ራስህ ብትመልሰው ይሻላል። ምክንያቱም ፖሊስ ስለሆነ ይጠቅማል ብለህ የመለመልከኝ አንተ ነህ። ጡረታ ከወጣሁ ደግሞ ዓመት አልፎኛል።» ብለዋል።

በማስከተልም የችሎቱ ጥያቄ «አዲስ አበባ መጥተው ከነሻለቃ ጌታቸው ጋር ምን ተባባሉ?» ብሎ ላቀረበላቸው የማጣሪያ ጥያቄ ምስክሩ በሰጡት ምላሽ ጥር/97 የመጣሁ ጊዜ የማራጀቱን ስራ በዚሁ ቀጥልበት አሉኝ። ሚያዝያ 97 ላይ ደግሞ የደረስኩበትን አስረደኋቸው» ብለዋል።

የአንደኛው የዐቃቤ ህግ የምስክርነት ቃል ተሰምቶ እንዳበቃ የሁለተኛው እና የሦስተኛው ምስክሮች በየተራ ችሎቱ ፊት ቀርበው በሰጡት ምስክርነት «ሚያዝያ 16 ቀን 1997 ዓ.ም ዋልታ ንጉስ፣ አስናቀ እና ሙሉ ጋሻ የተባሉ ተከሳሾች ስብሰባ ውጡ ካሉን በኋላ በስብሰባው ላይ ከዛሬ ጀምሮ አሸንፈናል ድምፅ የምትሰጡት ለሁለት ጣት ነው። ታጣቂም ሆነ ፖሊስ ከመጣ በያዛችሁት ዱላም ሆነ መጥረቢያ ቆርጣችሁ ጣሉት» ብለዋል። በዚህ ጊዜም ተሰብሳቢው «ብጥብጥ አንፈልግም እናንተ ደርግ ናችሁ ልብሳችሁን ቀይራችሁ ነው የመጣችሁት» ብሎ በመቃወም ስብሰባው እንደተበተነ

ለችሎቱ አስረድተዋል፡፡ እነዚህ ሁለት ምስክሮችም ለየብቻቸው በተራ በተራ ከተከሳሾች መሀል ዋልታ ንጉስ አስናቀንና ሙሉ ጋሾ የተባሉትን ተከሳሾች ለይተው አሳይተዋል፡፡ በዕለቱ የቀረቡት አራተኛው የዐቃቤ ህግ ምስክር በበኩላቸው ራሳቸውም የቅንጅት አባል እንደነበሩ ገልፀው ተስፋዬ ታሪኩ፣ ሙሉ ጋሾ እና ዋልታ ንጉስ አስናቀ የተባሉትን ተከሳሾች እንደሚያውቋቸው ገልፀው እነዚህ ተከሳሾች ከጥር/97 ጀምሮ የቅንጅት አደራጅ ሆነው እንደሚንቀሳቀሱ አስረድተዋል፡፡ ምስክሩ በማያያዝም ከላይ የተጠቀሱት ሦስት ተከሳሾች «የተነጠቁ እጆቻችንን በሰልፍም ሆነ በትግል ለማስመለስ የጦር መሳሪያ ይሰጣችኋል፡፡ እያንዳንዳችሁ ቤታችሁ መተኛት የለባችሁም፡፡ ከአምስት እስከ ስድስት እየሆናችሁ መከላከልና ማጥቃት አለባችሁ» ብለው እንደቀሰቀሷቸው የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዋልታ ንጉስ የተባለው ተከሳሽ መስከረም 8 ቀን 1998 ዓ.ም በግ አርዶ እንደሰበሰባቸውና በወቅቱም «በደጀን እጃችንን ለማስመለስ መስከረም 22/98 እጅ ለእጅ ተያይዘን እንውጣ» የሚል ቅስቀሳ እንዳደረገላቸው በዚህም ጊዜ አንድ ቄስ «እናንልቃለን ልታስጨርሱን ነው ወይ?» ብለው በሰጡት አስተያየት «እነሱ ያልቅላቸዋል» የሚል ዛቻ መሰንዘሩን ለችሎቱ አብራርተዋል፡፡

ችሎቱ የአራተኛውን ምስክር ቃል ካዳመጠ በኋላ «እርሶ የሚኖሩት የት ነው?» የሚል የማጣሪያ ጥያቄ አቅርቦላቸው ምስክሩ ነዋሪነታቸው ገጠር መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ችሎቱ የማጣሪያ ጥያቄውን በመቀጠልም «የሚኖሩት ገጠር ከሆነ ተከሳሾቹን እንዴት አወቋቸው?» ያላቸው ሲሆን ለዚህም በሰጡት ምላሽ «ተከሳሾቹ አደራጆቹ ናቸው እኛ ወዳለንበት ይመጣሉ እኛንም ስብሰባ ይጠሩናል» ብለዋል፡፡

በማስከተል የዕለቱ አምስተኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር ቀደም ሲል ምስክሩ ራሳቸው የመ.ኢ.አ.ድ አባል እንደነበሩ ገልፀው «ተስፋዬ ታሪኩ የተባለውን ተከሳሽ ከ 1995 ዓ.ም ጀምሮ አውቀዋለሁ፡፡ የመ.ኢ.አ.ድ አደራጅ ነበር፡፡ ነሐሴ 97 ላይ ይኸው ተስፋዬ የተባለው ተከሳሽ እኔንና አንድ ሌላ የቅንጅት አባልን ጠርቶን ኢህአዴግ ስልጣኑን ስለማይለቅ የታጠቀ ኃይል ማደራጀት አለብን፡፡ እኔ 15 የሚሆኑ ሰዎችን መልምዬ በማደራጀት ወደ በረሃ ልኬያለሁ፡፡ እናንተም አስራ አምስት አስራ አምስት ሰዎችን

እያደረጋችሁ አደራጅታችሁ በረሃ መግባት አለባችሁ፡፡» የሚል መመሪያ እንደሰጣቸውና በዚህም ጊዜ አብረዋቸው የነበሩት ግለሰብ የተደራጁት ምን ይበላሉ? ምንስ ይታጠቃሉ? የሚል ጥያቄ እንደቀረበ ተከሳሹ ተስፋዬ በበኩሉ ከውጭ ገንዘብ ይላክልናል ከአገር ውስጥም ገንዘብ ይገባልናል፡፡ ከዚህ ቀደም የመጣው አስር ሺ ብር ስላለቀ አሁን 400ሺ ብር ጠይቄያለሁ ይህን ገንዘብ ሲመጣ ከዛ ላይ እሰጣችኋለሁ፡፡» የሚል መልስ መስጠቱን ገልፀው አብረዋቸው ያሉት ግለሰብ ግን ቀደሞ ከመጣው አስር ሺ ብር ላይ ለኛ እንዴት አልተሰጠንም በማለት በገንዘብ እንደተጣሉ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡

የእኚህን ምስክር ቃል ተከትሎ ተከሳሽ ተስፋዬ ታሪኩ «እያደራጅን በረሃ እንላክ በሚለው ሃሳብ እርስዎስ ተስማምተው አልነበረም ወይ? ይህስ እርስዎን አያስጠይቆትም ወይ? ይህንን ጉዳይስ በምን ተፋርሰን ተውነው?» የሚል መስቀለኛ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ሆኖም ግን ዐቃቤ ህግ፣ ከዐቃቤ ህግ ዋናው ጥያቄ ጋር ተያያዥነት የሌለውና ምስክሩን ሊያስጠይቅ በሚችል ጉዳይ ላይ ጥያቄ ሊቀርብ አይገባም የሚል ተቃውሞ አሰምቷል፡፡ ችሎቱም ሊያስጠይቃቸው የሚችለውንና የማይችለውን ራሳቸው ምስክሩ ሊቃወሙ ይችላሉ፡፡ ስምምነት ላይ ያልደረሱበትን ወይም ከተከሳሹ ጋር የተፋረሱበትን ጉዳይ ግን ሊመልሱ ይገባል» በማለቱ ምስክሩ፣ ተከሳሹ ባቀረበው ሃሳብ ላይ አልተስማማንም አብሮኝ የነበረው ሰው ባቀረበው የገንዘብ ጥያቄ ምክንያትም ተፋርሰን ነው የተለያየነው የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ተከሳሹ ተስፋዬ ታሪኩ በማስከተልም «ለምን በሀሰት ይመሰክራሉ በምስራቅ ጎጃም ላይ የተፋረስነው ተስፋዬ ገንዘብ ስላጎደለ ነው ብለው በሰው ፊት ተናግረው የለም ወይ?» የሚል ተከታይ መስቀለኛ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ምስክሩ ለዚህም «በፍፁም አላልኩም ይህን ልልም አልችልም» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በዕለቱ በ6ኛ እና በ7ኛነት የቀረቡትን ምስክሮች አስመልክቶ ዐቃቤ ህግ ቀደም ብለው ከቀረቡት ምስክሮች ጋር ተመሳሳይ የሆነ ጭብጥ ስለሚያስረዱ አልፈልጋቸውም ባለው መሰረት ችሎቱ ይህንን ለቀሩት ሁለቱ ምስክሮች አስረድቶ ለመጪው ማክሰኞ የሌሎችን ምስክሮች ቃል ለመስማት ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡